“I have a dream.
One day, Hagos becoming the president of Oromia, Gemechu becoming the president of Tigray, Shemsu the president of Amhara... and we all laugh that we were once silly wasting our resources arguing about tribal issues that mixed up with politics”
#Ethiopia

ወዳጄ አብዱ አህመዲን በፌስ ቡክ ገጻቸው ያስፈሩት ሃሳብ ላጋራ ወደደኩ፣ ነገሩ ለአዲሱ ትውልድ ህልም ቢመስልም ያለፉትን 27 ሰባት የፖለቲካ፣ የታሪክ፣ ድንቁርናና የግል ፍላጎት ለማስፈጸም የተቃኘ ዝብርቅርቅ አመራር የፈጠረው አንጃግራንጃ መሰረተ ቢስነት ማሳየት ግድ ስለሚል ነው፣

ከአድዋ ድል ይሁን በዘመነ መስፍንት ዘርን ሳይሆን ኢትዮጵያዊነትን መሰረት ያደረገ ስብጥራዊ አመራር ነበር እንጂ ክቶውንም ቢሆን ዘርን ያማከለ በዘመኑ አባባል የዘር ሹመት አልነብረም፣በርግጥ በትግራይ; በወሎ፣ በሐረር፣ በወለጋ፣ በጎንደርና በሸዋ ፊዳላዊ ስርዓቱ ተክተሎ በሉዑላን በሉዕላን ቤተስቦች ወይም በአካባቢወ ታውቂ ስዎች ቤተሰባዊ ተዋርድ የተመደቡ አምራሮች ቢኖሩም፣ የለት ተለት አስተዳድራዊ ስራውን የሚያከናውኑ አስተዳዳሪዎች ግን በሞያችው እንጂ በዘር ሀርጋቸው እስክ 1983 ዓመተ ምህረት ተሾመው አያውቁም፣

በትግራይ እነ ድጃዝማች የማነ ሀስን፣ ደጃዝማች ዝናሀ ብዙመሳይ፣ በሲዳሞ እነ ራስ መንገሻ ስዩም፣ ደጃዝማች ዘውዴ ገበርስላሴ በአዲስ አበባ፣ ዶክተር በርከት( ከ1983 በሃላ ኤሬትራዊ) በሃረር  እነ አበበ ረታ እነ ዶክተር ስዩም ሃረጎት እነ ሌፍትናንተ ጀነራል መስፍን ገብረቃል፣ እነ ጀነራል አማን አምዶም በማዕከላዊ መንግሥት እንዲሁም በርካታ ስመጥር የኦሮሞ ተወላጆች እነ ጀነራል ጃጋማ ኪሎ፣ጀነራል ከብደ ገብሬ ስማቻው እዚህ ያለተንሳ ጀግኖቸ በተለየ በመከላካያና በፖሊስ ሰራዊት ካአጼ ምንሊክ ጀምሮ በዘራቸው ሳይሆን በሞያ በቃታቸው በመላ ሀገሪቱ ገዳጃቸው ተወጥትው ይህችን ሃገር እንደ ሃገር አቁሞዋታል፣

አድርባይ የታሪክ ጸሃፊዎች እንደሚሉትና እንዳሉት ሳይሆን ሁሉም በዘሩ ሳያፍር በኢትዮጵያዊነቱ ኩሩ ህዝብ መሆኑ በጋራ ለሃገሩ አንድነትና ነጻንት ዋጋ ከፍላል፣ በርግጥ አሰተዳደራዊ በደል ሲደርስበት በግልም በጋራም አምጻል ተፋልማል፣ ይህም በባሌ፣በጎጃም በትግራይ ተንስተው የነበሩ አምጾች መጥቀስ ይቻላል፣ ይሁንና ታሪክ እየተበረዘ የታሪኩ ባለቤትነት ሻሞ በሚያስብል ጨዋታ ዓይነት እየትቦጫጨቀ ለግል የፖለቲካ መጠቀምያ በመደረጉ የታሪኩ ባሌቤት ህዝብ አንተ ምን ታውቃልህ እኛ እንውቅልህ አለን የምንልህን ነው ታሪክ ማለት የሚሉ ሃስዊ መሲህ ዘምነኛ ፖለቲከኞች ያልስሙ ስም እያወጡለት ይገኛሉ፣

ከዘመናዩ ወያኔ ተብዬ ተያይዞ በስፊው የሚነሳው የትግራይ የወያኔ የ1940 ዎቹ አመጸ በጎጃም፣ በባሌ ክተነሳው አመጸ የተለየ ባህሪ የለውም፣ ጥያቄው የፍትህ፣ የግብር የቀነሰልኝ የሚልና ይዞ የወጣው ዓርማም ሆነ ያስማው ድምጽ ኢትዮጵያዊነቱን የሚኮንን አልያም ደብተራ ታሪክ ጸሃፊ ተበዬ እንደከተቡትና የውጭ ታሪክ ጸሃፊዎች ጭምር ያወናበዱብዱት በሬ ወለደ ተረት ተርት ጭራሽ አይገናኝም፣ በርካታ የጽሁፍና

ክትውልድ ወደትወልድ ቃል በቃል የወረደው ዑነት የሚሳያው በየትኛውም መመዘኛ  ፖለቲካዊ ይዘቱ ክምኒልክ ስልጣን መያዝና አስተዳደር ግኑኝነት እንዴሌለው ነው፤ ምክንያቱም ፖለቲካዊ ገጽታው ቀደም ብሎ በፖለቲካ ጋብቻ ዕልባተ አግኝቶ ነበርና፤

ይህን የምለው ወዳጄ አብዱ ህልሙ ህልም ብቻ አይደለም ዑነትና ዑነት ነው፤ በነገራችን የዚህ ዑነታ አድዋዎች እንዲህ ይላሉ " አድዋዊ የእህት ልጅ እንጂ የወንድም ልጅ የለውም ይላሉ" ይህም የነብረውን ነባራዊ ሁኔታ ሲገልጹ ነው፤ በአካባቢው ወታዳራዊ ካምፕ ስለነበረና አባላቶቹም ከመላ የሃገሪቱ ብሄር ብሄረስብ የተውጣጡ የሠራዊት አባላት ስለነበሩና ፤ የተፈጥሮ ጉዳይ ነውና ጋብቻ ሲፈጽሙ በብዛት ከአካባቢ ተወላጆች ስለነበር አባት ከየትኛውም ብሄር እናት የአክባቢው ተወላጅ ስለምትሆን ይህን አባባል እስከ ዛሬም የተለመደ አነጋገር ነው፤

ምንም እንካ በፖለቲካና ፖለቲኮኞች ዓይኔን ግንባር ያርገውና ህዝብን ህያው ፍጥረት የሚያስብ፤ የራሱና የማህበርስብ ውጤት መሆኑ አውቅው ይሁን ሆነ ብለው መካድና እንደግል ቁስ አካል ማየት የተለመደ ባህሪ ቢሆንም ቡዙዎቹ ታሪክ እያሽመደመደ ከፊሉ በቁሙ ከፊሉ ደግሞ ክሞት በኋላ የዘሩትን እያጨዱ ወደ ነበሩ ተቀይረዋል፤ መንግሥት ይመጣል መንግሥት ይሄዳል ህዝብ ግን ይቀጥላል በሚለው አባባል ጉዞው ቀጥላል ይቀጥላልም፤

ወደ ሃገራችን መለስ ብለን ስንቃኝ ከዚህ ዑነታ ውጭ አይደለም፤ መንግሥታት መጥተዋል ሄደዋል የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ነበር አለ ወደፊትም መኖሩን ይቀጥላል፤ በቅርብ ጊዜያት እንካ ያየናቸው መንግሥታት የኢትዮጵያ ህዝብን እንደግል ጉዑዝ ዕቃ እኛ በቀደድነው ቦይ መፍሰስ ካልቻላቹህ እየተብለ ጎራ እየለዩ ዋጋ እንዲክፍል አደርገውታል፤ የሚያሳዝነው ደግሞ ተቃዋሚ ነን፤ያሉ መንግሥት ተሳስቶታል ብለው ነፍጥ አነሳን ያሉቱንምና በለሰ ቀንታቸው በትረ ሥልጣኑ ሲጨብጡ ያኑኑ ያውገዙትን ድርጊት በዘመነና በረቀቀ ዜዴ አሽሞንሙነው መቀጠላቸው ነው፤

ይህም በሃገራችን የሚታይ ተጨባጭ ሁኔታ በሌሎች ታዳጊ ሃገራትም ቢታይም የኛ ግርምት የሚፈጥረው ከዕድገታችን ከታሪካችን ከማህበራዊ ዕሴታችን አንጻር ሲታይ ነው፤ ከብርና ምስጋና ለወላጆቻችንና ለአያቶቻችን የእምቢ አልገዛም ታሪክና በክርስትናም ሆነ በእስልምና ኀይማኖት የወረስናቸው ስነምግባሮች መነጽር ስንመልከተወ ነው፤ በብሄራቸው የማያፍሩ በኢትዮጵያዊንታቸው የማይደራደሩ ዘሮች ፍሬ ስለሆነ ነው፤

በርግጥ ከዘመን ዘመን ሁኔታዎች፤ አስተሳሰቦች ያድጋሉ፤ ከተክኖሎጂ ዕድገት፤ ከህዝብ ብዛት መጨመርና ክምርት ዕድገት መመናመን፤ ከተፈጥሮ ህብት ሚዛን መዛባት በስው ልጅ አስተሳስብ አናናር ለውጥ መጥታል እየመጣም ነው፤ ከትምህርት አስጣጣችን ጀምሮ መላ አስተሳስባችን፤ አናኖራችን፤ ፍላጎታችን ተለውጣል፤ ዘመን በወለደው ቴክኖሎጂ ከሌላው ዓለም ይበልጥ ተቀራርበናል፤ የባህል ወረራው እንዳል ሆኖ ለአዳዲስ አስተሳስብና አመለካከት ቅርብ ሆነናል፤

እዚህ ላይ ይህን ምቹ ሁኔታ ግን ሳንበላው እንዳይበላን ልብ ልንል ይገባል፤ ሁሉም ነገር በጎ ጎን እንዳለው ጎጂ ጎኑም ማጤን ያስፈልጋል፤ ለአንድ ስው የታዘዘ መፈወሻ ለሌላው መርዝ ሊሆን ይችላልና፤ ዛሬ ለበጎ የሚውጠኑ በውጉ ካልተያዙ ከጥቅማቸው ጉዳታቸው ያመዝንና ሃዲዱ ስቶ ካስብነው ሳይሆን ወደ ያልፈለግንው መዳራሻ ሊወስደን ይችላል፤ በአሁኑ ስዓት በተደረገው የዕርምት ለውጥ እንድተለመደው የዚህ ወይም የዚህ ማበረስብ ተጠሪ ነኝ የሚሉ ቡድኖች የሚያይሳዩት ምግብርና የሚረጩት ፕሮፖጋንዳ አዲሱና የነገው ተስፋ ትውልድ መንገድ እንድያስት ጥንቃቄ ያሻል፤

የትኛውም ቡድን መሰረታዊ በሆነው የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚ፤ የማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያለውን የታክቲክና የስትራተጂ አቅጣጫ ፖሊሲና መርህ አተኩሮ የህዝብን ላዕላዊ የድምጽ (የምርጫ) ውሳኔ ቢያተኩር ለሀገርም ለቡዱኑም ይበጃል፤ መናገረ ቀላል ነው ማድረግ ግን ከባድ ነው ማንም ይሁን ማንም በሚልዮን የሚቆጠር ህዝብ ፍላጎት ይቅርና የአነስተኛ ቤተስብ ፍላጎትም ማርካት ቀላል አይደለም፤ በማህበራዊ ድህረ ገጽ እንደመጻፍ፤እንደመሳደብ፤ በመርደረክ እንደማወረግረግ አልጋ ባአልጋ አይደለም፤

የምናውራው ስል አንድ ድሳሳ ጎጆ አይደለም በሚልዮን ስልሚቆጠር ባህል፤ታሪክ፤ ኩሩ ስብዕና ስላልው ህዝብና ቀጣይ ትውልድ ነው፤ ዛሬ የተከልናት ዛፍ እንድትጣመም ከፈቀድንላት ለቀጣዩ ትውልድ ለዘመናት

የማይወጣው የቤት ሥራ ጥለንለት እያለፍን መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፣ ሁላችንም በተለይ የስባዎቹ ዕድሜዎች የተሻገርን የአጭር ጉዞ መንግዶኞች ሞሆናችን አውቀን መቀመጫ እንዳናጣብብብ እያስተዋልን ብንጋዝ፣

ከሀገር ውጭ ሆኖነን በተራረፈቸው ስዓት ማህበራዊ ገጾችን የሙጥኝ ብለን ሀሳባችን የምንስንዝር ገንቢ በሆነ መልኩ ተጠቅመን ሀገራችንን ህዝባችንን ልንታደግ ይገባል። የተነበቡት መጻህፍት ካሉም ሀገራችን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር እያጣጣምን የነገዎቹ የትውልድ ባለ አድራዎች አቅጣጫ ብናሳይ ምክንያቱም በዛ ትውልድም እኛም በልጆቻችን በቤተቦቻችን ኢ-ሩቱዕ በሆነ መንገድ እንኖርበት አለን እኮ'፣ ይህን አለማድረግ “ምሳሌ አታርገኝ ምሳሌ ግን አታሳጣኝ” እንዲሉ በኢራቅ፣ በአፍጋኒስታ፣ በሊብያና በሶርያ ዳያስፖራ ከአሜሪካ መራሹ ጥቃት በኃላ የፈጸሙት ታሪካዊ ስህተት መማር ይኖርብናል።አዎን እንዚያ የየሀገሩ ተወላጆች ከያሉበት ተጠራርተው የተፈጠረው ሁኔታ ተከትሎ ሀገር ቤት ቢገቡም ምንም ሳይፈየዱ የአባትህ ቤት ሲወረር አብረህ .______________________________ እንዲሉ ህዝቡን ሜዳ ላይ በትነውና ማህብራዊ መሠረቱን አንገተው የያዙቱን ይዘው ወደ አስጠጋቸው ሀግሮች ነው የኮበለሉት።

አዎን ዲያስፖራ በሀገር ቤት ሊጫወታቸው የሚችሉ የመጫወቻ ሜዳዎች ቀላል የሚባሉ አይደሉም። ከሁሉም በላይ ዓለማችን በቴክኖሎጂ እየመጠቀች ኑሮና አናናራችን ብቻ ሳይሆን የስው ልጅ ራሱ ዲጂታላይዘድ ወደ መሆን በሚንጠራራበት ጊዜ በዚህ በኩል ያለንን ክፍተት የሞሙላት ግንባር ቀደም ሊሆን ይገባል። በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያሉ ቤተሶቦቻችን ኃላቀር በሆነ የእርሻ፣ የክብት አርባባብ ውይም አያያዝ፣ የንብ ማናባት ሲካቱኑ ይኖራሉ። በተጨማሪም እይኮስመነ ያለው የትምህርት ሥራዓታችን በመድገፍ ማዘመናን ብቁ ትውልድ በማፍራት የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር ሁኔታዎችን ማመቻቸትና መርዳት። እንዲሁም ሀንዶች፣ ፊሊፒኖች፣ ባንግላዲሾች ሌሎችም በኤሽያ፣ ግብጾች፣ ጋናዎች፣ ብራዚሎች፣ አርጀንቲናውያን እንዲሁም ሌሎች በአፍሪካና በላቲን አሜሪካ እንደሚደርጉት በመዋዕለ ንዋይ ማገዝ ያጠቃልላል።

አዎን በሀገራችንም ይሁን በሌላው አለም ፓርቲዎች በዓላማና በአመምላካከት ለበጎም ይሁን በጎ ላልሆነ ዓላማ በተሰባሰቡ ግለ ስቦች የቃቃማሉ እንጂ በምልዓተ ህዝብ ተቃቁምው አያውቁም። በመሆኑም ያዋጣናል በሚሉት ህዝብ፣ ብሄር፣ ርዕዮተ ዓለም ይምላሉ ይገዘታሉ። በፕሮፖጋንዳ፣ በፖልቲካ፣ በጥቅማጥቅም ከዚህ ባለፈም በጦር መሣርያ (በጉልበት) ተክታይ ያፈራሉ። የሂትልሩ ናዚ፣ የሞሶሎኒ ፋሽሽት፣ የዘመናችን አልካይድና አይሲስ በጎ ላልሆነ በሚልው ጎራ የሚመድው ሲሆኑ የኛዎቹ ጨምሮ ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት በኃላ አልቃይዳና አይሲስን ሳይጨምር የተፈጠሩት በብጎ ጎን ይታያሉ። ይህ ማለት በየሀገሩ ጽንፈኛ ዓላማ የሚያራምዱ የሉም ማለት ግን አይደልም። ይህ እንዳይ ሆን ሁላችንም ባህላችንን ታሪካችንን መስረት አድርገን ልንሰራ ይገባል።

በኛም ሀገር ወደድንም ጥላንም ታሪካችን ከዚህ ውጭ አይደለም። እላይ ለማለትና ለማሳየት እንደሞክርኩት በየጊዜው በፓርቲ ስም ይሁን በቡድን ብቅ ያሉት ክዚህ ሀቅ ውጭ አይደሉም። ድል አድረግን ያሉቱም ሆነ በትጥቅ ይሁን በስላማዊ ትግል ነበርን የሚሉት በዚሁ መንገድ የበቀሉ ናቸው።

እናማ ልብ ያልው ልብ ያድርግ እንዲሉ የራስን ማንነት በቀርርቶና በልበ ወለድ ታሪክ እያሽሞነምን ሌላውን እይኮነኑ ጉዞ ዋጋቢስንትና ሥልጣን ርስተ ጉልት እንዳልሁነ ሕይወትም ጊዜም የዱላ ቅብብሎሽ መሆኑ ልንቀብልና ልናግዝ ይገባናል። እኔ ወይም እኛ ከሌለን ይህ ጉዳይ አይሳካም ብሎ ማለትና ማስብ ድንቁርና ብቻ ሳይሆን ራስን በራስ የማጥፋት ያህል ነው።

ዛሬ ያለንበት ሁኔታ የሚጠይቀውን ያፈጠጠ ሀቅ መጋፈጥ ካልቻልን ማነንታችንን ቆም ብለን እንድንፈትሽ ግድ ይለናል። በነብር ጉዞ መራምድ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናልና። በተለይ በጊዜና በታሪክ አጋጣሚ ይነስም ይብዛም በትጥቅ ትግል ተሳትፎ የነበረው ሁሉ የስው ሥጋ እንደጥዋፍ ሲነድ አካሉ እንደ ብርጭቆና አለት ሲበታተን ያየ ዕውን ለህዝብ ዕኩልነት፣ለፍትህና ለዲሞክራሲ የተክፈለ መስዋዕትነት መሆኑ ካመነ ውለታ ጠያቂ መሆን ሳይሆን የታሪኩ የዱላ ቅብብሎሽ ውጤታማ እንዲሆን አጋዥ ኃይል መሆን ይገባዋል። አዎን በዚያ ዑንታ ያለፈ ሰው ለሥልጣንና ለንዋይ ጥቅም ያዙኝ ልቀቁኝ ካለ ቀድሞውንም በዓላማ ያልተቃኘ አንድም ሰው አረገ በሎ የተደባልቀ አልያም በነበረው ቀደምት የቆሸሸ ህሊና ለመሸሸ የተድባልቀ ከንቱ ነው።

ከዚህም ባለፈ ማንም ይሁን ማንም ከብሄር፣ ከዘር፣ ከጽኦታና ከቀለም ባሻገር የታሪክ፣የባህል የዘረ መል ቁርኝታችን በላይ ሰው መሆናችን ራሱ አንዳችን ላንዳችን እንድንቆም ተፈጥሮ ራስዋ ጎድን ትለን አለች። እንዲህ ነኝ እንዲህ ነበርኩ ለማናችንም አይብጅም። ስደት ለውሬ  ያመቻል እንዲሉ በትፈጠረው አጋጣሚ ወደ ሀገር ቤት የተመለሳቹሁም ምንም አድረጉ ምንም ሀዝቡ የሚጠብቀው የዛሬ ሥራቹህ ነውና በተግባርና በቅንነት ስርታቹሁ አሳዩት። እነ ዘርዓይ ደርስና አብዲሳ አጋ በጣሊያን ያደረጉት ተጋድሎ ለፍትህ ለኩልነት እንጂ የዜግነት ወይም የተወላጅነት አብዜ አስገድዶአችው አልያም ሀገር ቤት የሚጠብቃቸው ሹመትና ማዕርግ አልነበረም። ባንዴራችው ህዝባቸው መደፍሩ በሰው ሀገርም ቢሆን ስብዓዊ ፍጡር መብደሉ ሲመልከቱ አላስችል ሰለ አላስቾላው እንጂ። ዛሬ መንደርና ጎጥ ላይ የኛ ሙጥኝ ማለት የነዚህን ጀግኖች ትግል ማራከስ ነው።